፫/ የቦርድ ሰብሳቢው በሚኖርበት ጊዜ የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡ እርሱ ባልተገኘ ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ስብሰባዎችን ይመራል ወይም ሁለቱም ባልተገኙ ጊዜ ሰብሳቢው በወከለው የቦርድ አባል ስብሰባው ይመራል፡፡

፬/ የቦርድ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ሰብሳቢው ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በእርሱ የተወከለ ሰው ወይም የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከቦርዱ አባላት ሦስቱ ሲጠይቁ ስብሰባው በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡

፭/ ማንኛውም የቦርድ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፡፡ ቦርዱ በድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፮/ የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤዎች በትክክልና ቦርዱ በሚወስነው አኳኋን ይመዘገባሉ፡፡ በቦርዱ ካልተፈቀደ በቀር ቃለ ጉባኤዎች በምስጢር ይጠበቃሉ፡፡

፯/ ከፈንዱ ሥራ ጋር የሚጋጩ የግል ጥቅሞች ያሉት የትኛውም የቦርድ አባል ይህንኑ በጽሑፍ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፣ በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ በሚደረጉት የቦርድ ውይይቶችም አይሳተፍም፡፡

## ፲፪. የቦርድ አሠራር

፩/ ቦርዱ የራሱን የአሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቦርዱ ውሳኔዎቹን ለማቀላጠፍ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## ፲፫. የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹመት

፩/ የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ በብሔራዊ ባንክ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማሉ፡፡

3/ The Chairperson shall, whenever present, preside over meetings of the board. In the absence of the Chairperson, Deputy Chairperson shall preside over such meetings or in absence of both Chairpersons a board member of the Fund, who is designated for this purpose by the Chairperson, shall preside over such meeting.

4/ Meeting of the Board shall be held at least once every three months; provided, however, that the Chairperson or, in his absence the person delegated by him, may call a meeting at any time or when the Chief Executive Officer of the Fund or three board members so request.

5/ All decisions of the Board shall be made by a simple majority vote of the members present. In case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

6/ Minutes of meetings of the Board shall be recorded accurately and in such form as the Board may determine. Unless the Board decides otherwise, minutes of the Board shall be confidential

7/ A Board member shall disclose to the Board in writing any personal interests in the activities of the Fund and shall not be present in the deliberations of the Board in respect of that matter.

## 12. The Board Procedure

1/ The Board may adopt its own rules of procedure.

2/ The Board may establish a committee to facilitate its decisions.

## 13. Appointment of Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officer of the Fund

1/ A Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officer of the Fund shall be appointed by the Government as recommended by the National Bank.

**፲፭. የፈንዱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር**

የፈንዱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ የፈንዱን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይረዳል፡ የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በሌለ ጊዜ ለፈንዱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የተሰጡትን ሥራዎች በሙሉ ያከናውናል።

## ክፍል ሶስት

## ፋይናንስ ነክ ድንጋጌዎች

**፲፮. ስለአረቦን ክፍያ**

፩/ ሁሉም አባል የፋይናንስ ተቋማት ይህ ደንብ ሥራ ላይ በዋለ በ፴ ቀናት ውስጥ ከፈንዱ ጋር የአባልነት ውል ተፈራርመው በፈንዱ የሚወሰነውን መነሻ የዓረቦን ክፍያ ወደ ፈንዱ ሂሳብ ገቢ ያደርጋሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚደረገው መነሻ የዓረቦን ክፍያ የፈንዱ መነሻ ካፒታል ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መነሻ የዓረቦን ክፍያ ባይፈጸም ፈንዱ በቀሪው የገንዘብ መጠን ላይ ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ የቅጣት ምጣኔ ይጥላል፡፡ የቅጣት ምጣኔዉ በፈንዱ ይወሰናል፡፡

፬/ ተጨማሪ መነሻ ካፒታል እንዲሆን መንግሥት ብር ፪፻ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) ለፈንዱ ይመድባል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የአባልነት ውል የፈረሙ ሁሉም አባል የፋይናንስ ተቋማት የአማካይ ተቀማጭ ገንዘባቸውን 0.3 በመቶ ዓመታዊ የዓረቦን ክፍያ ለፈንዱ ይፈጽማሉ፡፡

፮/ ጤናማ ያልሆነ የፋይናንስ ተቋም ስለሚፈፅመዉ የተለየ መነሻ የዓረቦን ክፍያ ፈንዱ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

**15. Powers and Duties of the Deputy Chief Executive Officer of the Fund**

The Deputy Chief Executive Officer of the Fund shall assist the Chief Executive Officer of the Fund and in the absence of the Chief Executive Officer of the Fund shall discharge all the functions conferred on the Chief Executive Officer of the Fund.

## PART THREE

## FINANCIAL PROVISONS

**16. Payment of Premium**

1/ All member financial institutions, within 30 days from the effective date of this Regulation, shall sign membership contract with the Fund and pay to the Fund's account an initial premium to be determined by the Fund.

2/ The initial premium contributed in line with Sub-Article (1) of this Article shall be considered as initial capital of the Fund.

3/ In case that the initial premium is not paid within the time specified in Sub-Article( 1) of this Article, the Fund shall charge default interest rate on the due amount for the period of delay. The default interest rate shall be determined by the Fund.

4/ The Government shall contribute Birr 200 Million (Two Hundred Million Birr) to the initial capital of the Fund.

5/ All member financial institutions that signed membership contract as per Sub-Article (1) of this Article shall pay to the Fund annual premiums of 0.3% of their average deposits.

6/ The Fund may determine by a directive a special initial premium to be paid by a financial institution with poor financial soundness.

## ክፍል አምስት

## አባልነትና በመድን የተሸፈነ የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ

### ፳፬. የፈንዱ አባልነት

፩/ የትኛውም የፋይናንስ ተቋም በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የፈንዱ አባል ይሆናል፡፡

፪/ ይህ ደንብ ከወጣ በኋላ የሚመሠረት የፋይናንስ ተቋም የፈንዱ አባልነት ተቋሙ የሥራ ፈቃድ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የፈንዱ አባል የሚሆን የፋይናንስ ተቋም በፈንዱ የሚወሰነውን መነሻ የዓረቦን ክፍያ ይፈጽማል፡፡

፬/ የአባል ፋይናንስ ተቋማት መብቶችና ግዴታዎች ፈንዱ ከተቋማቱ ጋር በሚገባው የአባልነት ውል ውስጥ በዝርዝር ይገለፃል፡፡

### ፳፭. ከአባልነት ስለመሰናበት

፩ / ማንኛውም አባል የፋይናንስ ተቋም፡-

ሀ) የተሰጠው የሥራ ፈቃድ በብሔራዊ ባንክ ተመላሽ ከተደረገ፣ ከተሰረዘ፣ ወይም ከተነጠቀ፡

ለ) በፋይናንስ ተቋሙ ላይ የመፍረስ ውሳኔ ከተላለፈበት፡

ሐ) የአባል የፋይናንስ ተቋም ተቀማጭ ገንዘቦች ሙሉ በሙሉ ወደ ሌላ የፋይናንስ ተቋም ከተላለፉ፡

መ) በአባል የፋይናንስ ተቋም በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመፍረስ ጥያቄ መሠረት የንብረት አጣሪ ከተሾመ፡

ሠ) አባል የፋይናንስ ተቋም ከሌላ የፋይናንስ ተቋም ጋር ሲቀላቀል ወይም ሲዋሃድ፡ ወይም



## PART FIVE

## MEMBERSHIP AND PAYMENT OF INSURED DEPOSITS

### 24. Membership of the Fund

1/ Any financial institution shall be a member of the Fund according to the conditions laid down in this Regulation.

2/ Membership of a financial institution that is established after the effective date of this Regulation shall start on the date of issuance of the business license.

3/ The financial institution becoming a member of the Fund under Sub-article (2) of this Article shall pay a fixed initial premium to be determined by the Fund.

4/ Rights and obligations of the member financial institutions shall be laid down in a membership contract to be signed between the Fund and the member financial institutions.

### 25. Cessation of Membership

1/ A financial institution shall automatically cease being a member of the Fund upon:

a) surrender, cancellation or revocati on of a member financial institutio n license by the National Bank;

b) issuance of a winding-up order against the member financial institution;

c) transfer of all deposit liabilities of a member financial institution to any other financial institution;

d) appointment of a liquidator in pursuance of a resolution for the member financial institution voluntary winding up;

e) merger or amalgamation of the member financial institution with any other financial institution; or

**፵፩. ቅጣት**

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛዉም ሰዉ ፈንዱ በሚያወጣዉ ዝርዝር መመሪያ መሠረት እስከ ብር ፲ሺ (አሥር ሺ ብር) እና ጥሰቱ ለተከሰተበት ለእያንዳንዱ ቀን እስከ ብር ፩ሺ (አንድ ሺ ብር) ይቀጣል፡፡

**፵፪. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**፵፫. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፱ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**41. Penalty**

Any person who contravenes the provisions of this Regulation shall be punished with a fine not exceeding Birr 10,000 (Ten Thousand Birr) and shall be subjected to a daily penalty not exceeding Birr 1,000 (One Thousand Birr) for every day the contravention continues based on the detail directive to be prescribed by the Fund.

**42. Inapplicable Law**

No regulation, directive or practice may, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this Regulation.

**43. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 16th Day of February, 2021.**

**ABIY AHMED (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት